**ደረሰ አየናቸው፤ *ሰሎሞናውያን፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ታሪክ (1262-1521)* (አዲስ አበባ፣ ጃጃው አሳታሚዎችና ዴቨሎፐረስ ኃ. የተ.የግ. ማ.፣ 2013 ዓ.ም.)፤ የገፅ ብዛት 376፤ ዋጋ 200 ብር።[1]**

የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክን በማስተማር እና ምርምር በማድረግ ላይ ከተሰማሩ ጥቂት ኢትዮጵያዊያን የታሪክ ባለሙያዎች መካከል አንዱ የሆነው ደረሰ አየናቸው *ሰሎሞናውያን የኢትዮጵያ መንግሥት ታሪክ (1262-1521)* በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ በ2013 ዓ.ም. አሳትሞ ለአንባቢዎች አቅርቧል። ይህ በታሪክ ባለሙያ ተዘጋጅቶ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበው መጽሐፍ የዚህ ግምገማ ትኩረት ነው።

ከ13 እስከ 16ኛው መ.ክ.ዘ. የኢትዮጵያ ታሪክን በተመለከተ በ1972 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በታደሰ ታምራት፣ በ1984 ዓ.ም. በስቴቨን ካፕላን፣እና በ2003 ዓ.ም. በማሪ ሎር ዶራ የቀረቡት ጥናቶች በዘርፈ-ብዙ አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ፣ ወታደራዊ፣ እና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የታሪክ እውቀት አበርክተዋል። የደረሰ መጽሐፍም በዚሁ የጊዜ መደብ ላይ ያተኮረ ሆኖ የነገሥታቱን ታሪክ ነጥሎ ከማቅረብ ይልቅ በሰሎሞናዊ ስርወ-መንግስት ታሪክ ላይ በማተኮር ከ1262 እስከ 1521 ዓ.ም. የሚሸፍን ሲሆን ይኀውም ቀዳማይ ትውልድ የሸዋ ሰሎሞናዊያን የንግሥና ዘመን ነው።

ደራሲው የሰሎሞናዊያንን ታሪክ ከቅድመ-አክሱም የጀመረና ያልተቋረጠ ሥርዓተ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ያስቀምጠዋል። ነገሥታቱንም የደአማታዊያን፤ አክሱማዊያንና ድህረ-አክሱም ‹‹ዛጕዌ-ሰሎሞናዊያን›› ወራሽ ያደርጋቸዋል። ሰሎሞናዊያን በኃይልና በዛሬው ቋንቋ ፕሮፓጋንዳ በምንለው ስልት የተረከቡትን ሥርዓተ-መንግሥት የርዕዮተ-ዓለም፤ ባህል እና እምነት የመወራረስ ሂደት ያስረዳል። የስርዓተ-መንግሥቱ ቀጣይነት ላይ ክርክር የሚቀርብበትን በድህረ-አክሱም እና ቅድመ-ዛጕዌ መካከል ያለውን በመረጃ እጥረት በሚገባ ያልታወቀ ‹‹ድንግዝግዝ›› ዘመን ይለዋል። ሰሎሞናዊያን በዛጕዌ ነገሥታት ላይ የሚያቀርቡትን ህገ-ወጥ ንግሥና ክስ ደግሞ ‹‹ዛጕዌ-ሰለሞናዊያን›› ብሎ በሰየመው በቅርብ አመታት እየጎለበተ የመጣውን የምሑራን ኃሳብ ያቀርባል።

በእስልምና፤ አይሁድ እና ነባር እምነት ላይ ተመስርተው ይገዳደሩ የነበሩትን ግዛቶች ለክርስቲያኑ መንግሥት ነገሥታት እንዲገብሩ ለማድረግ የተደረጉት ወታደራዊ ዘመቻዎች የሰሎሞናዊያን ግዛት የማስፋትና ጠንካራ ክርስቲያናዊ መንግሥት ምሥረታ ታሪክ አካል ሆነው ቀርበዋል። ደራሲው ከ13ኛው እስከ 16ኛው መ.ክ.ዘ. ከነገሡ ሰሎሞናዊያን መካከል አፄ አምደ ጽዮን የግዛት ማስፋፋት ‹‹መሐንዲስ›› እንደሆነ ገልጾ ንጉሡ ወደ ክርስቲያኑ መንግሥት በወታደራዊ ዘመቻ ያካተታቸውን የሰሜን፤ ሰሜን ምዕራብና ምሥራቅ ግዛቶች ይዘረዝራል። የዘመቻዎቹን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ ላይ ተመስርቶ አፄ አምደ ጽዮን ባለብዙ ብሔር የክርስቲያን መንግስት ለወራሾቹ ማስተላለፉን ያስረዳል። ወራሾቹም ንጉሡ ያካተታቸውን ግዛቶች ማስጠበቅ፤ በአይሁድ እና ነባር እምነት ተከታይ መሪዎች የሚመሩ ተፎካካሪ ኃይሎችን የማስገበርና ሕዝቡንም በክርስትና የማጥመቅ፤ በእስልምና የሚመሩትን በፖለቲካ ስልት ውስጣዊ አንድነታቸውን የማዳከም፣ ካልሆነም ወታደራዊ ዘመቻ በማድረግ

[1] ይሕ የመጽሐፍ ግምገማ ሲዘጋጅ ሞክሼ ሆሄያትን በተመለከተ የዎልፍ ሌስላውን የእንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት ተጠቅሟል። ከዚህ በተጨማሪም የአውሮፓውያንን ዘመን መቁጠሪያ የሚጠቀም ሲሆን እ.ኤ.አ. በሚል ተመላክቷል።

ግብር መክፈላቸውን እንዲቀጥሉ ማድረጋቸውን ያትታል። በዚህ ረገድ የአፄ ሰይፈ አርዕድ (1344—71) እና አፄ ዳዊት(1380-1413) ከኢፋት ወላስማ ሱልጣኖች ጋር፣ አፄ ይስሐቅ (1414—29/30) በስሜን፤ ጸለምትና ወገራ ከይሁዲ ራስ ገዝ መሪዎች ጋር፣ እንዲሁም አፄ ዘርአ ያዕቆብ (1434-68) ራሱን ካደራጀው የአዳል ሱልጣኔት መሪ ከነበረው አህመድ በድላይ ጋር ያደረጓቸውን ትንቅንቆችና ጦርነቶች አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ አንድምታዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ሰለሞናዊያን በነባሮቹና በተስፋፉባቸው ግዛቶች ስለተከሉት የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓትና ያስተናገዳቸው ለውጦች በተመለከተ የቀረበው ዘለግ ያለ ትንታኔ የዚህ መጽሐፍ አንዱ ፋይዳ ነው። በዚህ ዙሪያ በታደሰ ታምራት፤ ሞርድካይ አቢርና ዲሚትሪ ቱብኪስ የተሰሩት ምርምሮች ጋር ይናበባል። ደራሲው በታደሰ ታምራት ንድፈ ኃሳብ ላይ በመንተራስ የመካከለኛው ዘመን ክርስቲያናዊ የመንግስት አስተዳደር መንተያ አመራር ስለሆኑት ማእከላዊና ክልላዊ አስተዳደሮች ያስረዳል። ሞርድካይ አቢር የሰሜን፤ የደቡብ እና የምስራቅ ግብር ከፋይ ግዛቶች ብሎ የከፈላቸውን የክልላዊ አስተዳደሮች አመዳደብ በመከተልና በዋናነት በዚሁ ጥናት ላይ በመመርኮዝ በእነዚህ ግዛቶች የነበረውን በንጉሡ ይሁንታ፤ በወታደራዊ አስተዳደር እና ግብር በማስከፈል የሚተገበሩትን የአስተዳደር ዘዬዎች ይነግረናል። የፖርቱጋላዊውን ፍራንቸሽኮ አልቫርሽ የኢትዮጵያ ቆይታ ግሩም ዘገባ፣ በሽሀባዲን አህመድ/አረብ ፋቂህ የተጻፈውን የኢማም አህመድ የጦር ዘመቻ፣ ጣሊያናዊው ኢኛዚዮ ጉይዲ ምርምር ያደረገባቸው ነገሥታቱን የሚያሞግሱ ግጥሞች የያዙትን ታሪካዊ ሰነዶች፣ እና ታሪከ-ነገሥት የመሳሰሉትን ቀዳማይ መረጃዎች ላይ በመንተራስ ከላይ በተጠቀሱት የክልሎች አስተዳደር ብቻ ሳይሆን በሰሎሞናዊያን ተዘዋዋሪ መቀመጫ ስለሆነው ከተማ-ንጉስ የነበረውን የመንግሥት አስተዳደር ያስረዳል። ደራሲው ከ14ኛው እስከ 16ኛው መ.ክ.ዘ. የነገሥታቱ ከተማዎች ላይ የፍልስፍና ዲግሪ ማሙያ ጥናት ማድረጉ ዘርፈ-ብዙ እገዛ እንደሚያደርግለት ይታመናል።[2]

በመንግሥት አስተዳደር ሥልጣንን በተመለከተ የነገሥታቱ ‹‹መለኮታዊነት›› እሳቤ ያስከተለውን አስተዳደራዊ ተፅዕኖ ይነግረናል። በበዓለ-ሲመት (ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ጀምሮ በስርዓተ-ቍርሐት) መለኮታዊ ኃይልን የሚያጎናፅፈውን የሰሎሞናዊያንን ዙፋን የሚረከበው ንጉሥ በወታደራዊና ሲቪል ጉዳዮች ፍጹማዊ ስልጣን እንደሚኖረው፤ ይህ መለኮታዊ ስልጣን የታሪክ ሰነዶች ‹‹ህዝቡን ከጥፋት ለመታደግ፣ ሲያስፈልግም ሕይወቱን ለሕዝቡ አሳልፎ ለመስጠት የተቀባ ባለአደራ››(122) አድርገው እንደሚያቀርቡት ይነግረናል። በዚህ ጉዳይ ላይ ዋና የመረጃ ምንጮቹ የአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዜና መዋእልና በንጉሡ የተፃፉ ድርሳናትን ናቸው። የአፄ ዘርአ ያዕቆብ ስብእና እና አስተዳደር ዘመን ስለመለኮታዊ ስልጣን ትንታኔ ለመስጠት ሞዴል መሆኑ ተገቢ ነው።

ይሕ መጽሐፍ ስለ ሰሎሞናዊያን የጦር ሠራዊት አደረጃጀት የሚያቀርበው ታሪክ ስለመካከለኛው ዘመን የመንግሥት አስተዳደር ለመረዳት በእጅጉ ያግዛል። በንጉሥ እና ብሕት ወደድ ሥር የሚደራጀው ከፍተኛ የጦር ክፍል፤ ተዘዋዋሪ የጨዋ ሠራዊት እና የክልል የጦር

[2] Deresse Ayenachew, "Le *kätäma.* La cour et le camp en Éthiopie (XIVe–XVIe siècle): Espace et pouvoir," PhD Dissertation, University of Paris I Panthéon-Sorbonne, 2009.

ሠራዊት የያዘው ባለሦስት ረድፍ የጦር አደረጃጀት የዘመኑ የአስተዳደር ጉዳዮች አስፈፃሚነት ሚና ያብራራል፡፡

ዋነኛው የጦር ሠራዊት የሆነው የጨዋ ሠራዊት ክልልን ከማእከላዊ መንግሥቱ በማገናኘት ‹‹የመንግሥት አስተዳደር ምሰሶ›› እንደነበረ ይገልጻል፡፡ ከአምደ ጽዮን ጀምሮ በተጻፉ ዜና መዋእሎችና ሌሎች ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ላይ በመንተራስ የሰሎሞናዊያንን የጦር አደረጃጀት፣ የጨዋ ሠራዊት አመራር፣ የሠራዊቱ በፖለቲካ ሽኩቻዎች ውስጥ ጣልቃ መግባት፣ እና አመፅ ይነግረናል፡፡ ይህ የጦር አደረጃጀት በአፍሪካ ቀንድ ለሁለት መቶ አምሳ አመታት የዘለቀ የኢትዮጵያ መካከለኛው ዘመን መንግሥት አስተዳደር እንዲፈጠርና እንዲፀና ቁልፍ ሚና እንደተጫወተ እንረዳለን፡፡ የጨዋ ሠራዊትን አደረጃጀት፣ ዝርዝር አስተዳደራዊ ሚና፣ እንዲሁም በጊዜ ሂደት መጠናከርና መዳከም ለማብራራት የሚያስችሉ የታሪክ ሰነዶች ውስን መሆናቸው ጸሐፊውን ጠቅለል ባሉ ገለጻዎች ላይ እንዲታጠር ቢያስገድደውም በዚህ ተጨማሪ ምርምር  በሚያስፈልገው ጉዳይ ላይ መነሻ የሚሆኑ ምልከታዎችን ይጠቁማል፡፡

በታሪክ ጥናቶች ላይ በወታደራዊና ፖለቲካዊ የአስተዳደር ታሪክ ጥናት አምድ ስር ተከልሎ ወይም ችላ ተብሎ የሚታለፈውን የሲቪል አስተዳደር ታሪክ ማቅረቡ የመጽሐፉ ጥንካሬ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይሁንና የወታደራዊና ሲቪል ሚና መደራረቦች የተለመዱ በመሆናቸው የሲቪል አስተዳደርን በተናጠል ማቅረብ ንድፈ-ኃሳባዊና የመረጃ ትንተና ተቃርኖ ስለሚፈጥር፤ እንዲሁም የከተማ-ንጉሥና የክልሎች ሲቪል አስተዳደሮች ውስብስብነት ለማስረዳት የመረጃ ምንጮች ውስንነትና ግልፅ ያለመሆን ችግሮች ደራሲውን እንደፈተኑት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የተሻለ መረጃ የሚገኝበትን የአፄ ዘርአ ያዕቆብ እና አልቫርሽ የዘገበውን የልብነ-ድንግል ዘመን ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ደራሲው ‹‹ዝርዝር የሥራ ዘርፎችን ለመተንተን ራሱን የቻለ መጽሐፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል››(156) በማለት የመካከለኛው ዘመን ሲቪል አስተዳደር ታሪክ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ተጨማሪ ምርምሮች እንደሚያስፈልጉ ይጠቁማል፡፡

ይህንን ከላይ የተገለጸውን የመካከለኛው ዘመን የአስተዳደር ስርዓት በተመለተከ ያደረገውን ጥናት  የግዛቶች አስተዳደር መዋቅሮችና ለውጦችና በማሳየት ይደመድማል፡፡ በዚህ ረገድ የቀጥታ፣ ተዘዋዋሪ፣ እና ግብር-ከፋይ ግዛቶች አስተዳደር ዘይቤ የሚተገበርባቸውን ግዛቶች ከሰሜን ኤርትራ-ምጽዋ እስከ ባሊ ድረስ የተከሰቱ አበይት የአስተዳደር ሁነቶችን እጅግ ውስን ከሆኑት መረጃዎች ላይ በመልቀም ለማብራራት ይሞክራል፡፡ በእነዚህ ግዛቶች የነበረውን ውስጣዊ አስተዳደር በተመለከተ የአፄ ዘርአ ያዕቆብ-በእደ ማርያም ዜና መዋእል እና የአልቫርሽ ዘገባ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህም የታሪክ ሰነዶች እጥረት እንዳለ ሆኖ በየግዛቱ የነበረውን እጅግ ውስብስብ የአስተዳደር ሁኔታ መሰነድ ፈታኝነቱ አይካድም፡፡

የሰሎሞናዊያን መንግሥት ከክርስትና እና ቤተ-ክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት፣ እንዲሁም የሰሎሞናዊያን ደጋፊ ገዳማት ፖለቲካዊ ሚና በተመለከተ የቀረበው ትንታኔ በአብዛኛው በነባሩ የቤተ-መንግሥትና ቤተ-ክህነት ግንኙነት ምርምር የታወቀ ነው፡፡ የደራሲው ትኩረት በመንግሥት ታሪክ ላይ መሆኑ እምነቶችና ተቋማት የነበራቸውን ፖለቲካዊ ሚና እንዲፈትሽ አድርጎታል፡፡ በዚህ ክፍል ላይ የ15ኛው መ.ክ.ዘ.  የአፄ ዘርአ ያዕቆብ ክርስቲያናዊ ብሔርተኝነት በክርስትና የለውጥ ቡድኖች፣ ነባር እምነት ተከታዮች፣ እና ተፎካካሪ የፖለቲካ ኃይሎች ላይ ያስከተላቸው ውጤቶች፤ የንጉሱ የነባር እምነቶች እገዳ የነበረው ሐይማኖታዊና

ፖለቲካዊ ፋይዳ፤ የንጉሡ ‹‹የክርስትና እምነትን የማፅናት›› ኃይማኖታዊ እንቅስቃሴ የነበረውን ፖለቲካዊ ሚና ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

የክርስትናን፤ ቤተ-ክርስቲያንንና ክርስቲያን ስብዕናዎችን ፖለቲካዊ ሚና በአንድ አውድ የማቅረብ ዝንባሌ ቢታይም የቀረበው ዳሰሳ ግን የሰሎሞናዊያንን መንግሥት ስላፀኑና ስለፈተኑ ኃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ፖለቲካዊ ጉዳዮች በማስረዳት ረገድ መልካም አስተዋፅዖ አለው፡፡

ከፖለቲካዊ፤ ወታደራዊ እና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች በተጨማሪ ስለሰሎሞናዊያን መንግሥት የኃብት መሠረት፤ የኢኮኖሚ ስርዓትና አስተዳደራዊ ጠቀሜታዎች መረጃ መስጠቱ የዚህ መጽሐፍ ሌላው ጠንካራ ጎን ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የመንግሥት ዓበይት የገቢ ምንጭ የሆኑትን የርስተ-ጉልት መሬት ስሪት፣ የንግድ ኬላዎች እና ግብር በታሪክ ምርምር ውጤቶች በማስደገፍ ያብራራል፡፡ የመሬት ይዞታ መብት አስተዳደርን ሲገመግም የኢትዮጵያ የመካከለኛው ዘመን ‹‹በየትኛውም መስፈርት ፊውዳል የተባለውን የመንግስት ስርዓትን አያመለክትም›› (259) በማለት ይሞግታል፡፡ በዋናነት በአልቫርሽ መፅሐፍ ላይ በመንተራስ የመንግሥት ሹሞች በመሬት ላይ የነበራቸውን ስልጣን ውስንነት ከግምት አስገብቶ የሰሎሞናዊያን ፖለቲካል ኢኮኖሚ መሠረት ፊውዳላዊ እንዳልነበረ ያስረዳል፡፡ በእርግጥ ይህ ጉዳይ ለዘመናት ምሑራንን ያከራከረ ሲሆን ደራሲው ባቀረበው ሙግት ልክ ስር ለመስደድ ከንጉሠ ነገሥት እስከ ገበሬው ድረስ የተዘረጋ ተዋረዳዊ የስልጣንና የኃብት ሥርዓት፤ የመሬት ይዞታን መሠረት ያደረገ ሥልጣንና ኃብት፤ የባላባቶች በገበሬው ምርት ላይ ያላቸውን ስልጣን የተመለከተው የምርት ግንኙነትና ሌሎች የፊውዳዝም ደገፍ ምሁራን የሚያነሷቸው ክርክሮች ላይ ጠንከር ያለ ምርምርና ተጨማሪ መረጃዎች ማቅረብ ይጠይቃል፡፡ ይሕ የፊውዳሊዝም ጉዳይ በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ አውድ ውስጥ በተሻለ የመረጃ አቅርቦትና እየጠሩ በመጡ ንድፈ ኃሳባዊ ክርክሮች እየታሸ ቀጣይነት ያለው ክርክር የሚደረግበት ነው፡፡ ይሁንና የታሪክ መረጃዎች ውስንነት ስለ መካከለኛው ዘመን ደርዝ ያለው ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

የሰሎሞናዊያን በግብር ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚን ሲያብራራ የግብርን ምጣኔ ኃብታዊ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ፋይዳ ይገመግማል፡፡ ከዜና መዋእሎችና ሌሎች የመረጃዎ ምንጮች በተጨማሪ የብርብር ማርያም የታሪክ ሰነድ እና ስርዓተ-ግብር የተባለውን ከአፄ አምደ ፅዮን ጀምሮ የተሰራ የግብር ሕግ ሰነድ ላይ በመመርኮዝ በዋናነት የ15ኛውንና 16ኛው መ.ክ.ዘ. የግብር አሰባሰብ ስርዓት፣ ከተለያዩ ግዛቶች የሚገቡ የግብር አይነቶች፣ ስለ ውዝፍ ግብር፣ ግብር ክልከላ የሚያስከትለውን ፖለቲካዊና ወታደራዊ መዘዝ፣ እንዲሁም የግብር ሰብሰቢዎች የማዕረግ ስምና ኃላፊነቶች ያስረዳል፡፡ በመጨረሻም ‹‹የርስተ-ጉልትና የግብር ሥርዓቶች ላይ በመንተራስ ሰሎሞናዊያን አንድ ጠንካራ የመካከለኛው ዘመን መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ለመመስረት ችለዋል›› ይለናል፡፡ (280) ይህ በሰሎሞናዊያን መንግሥት የምጣኔ ኃብት ስርዓት ላይ የተደረገው ጥናት በቂ የታሪክ መረጃዎች አለመኖር ባያግደው ከታሪካዊ ዳሰሳ ያለፈ እውቀት ማካፈል ይችል ነበር፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ደራሲው ደጋግሞ የሚጠቅሰው የ‹‹ጠንካራ መንግሥት›› ጉዳይ አከራካሪነቱ አይካድም፡፡

ደራሲው መጽሐፉን የሚደመድመው ‹‹የአዜባዊነት ተምኔታዊ ርእዮት እና የብሔረ ኢትዮጵያ መወለድ›› የሚል ርዕስ በሰጠው ምዕራፍ ነው፡፡ ‹‹አዜባዊነት›› በክብረ ነገሥት ላይ የሚታወቀውን የንግሥተ-አዜብ ትውፊትን ተንተርሶ የሚቀርበው ትርክት ነው፡፡ ክብረ ነገሥት

በዋናነት ተገዳዳሪ የሥልጣን እጩዎችን መከልከያ እንዲሆን ሲታሰብ ጥቅም ላይ እንደሚውልና፣ ሥልጣን ለያዙት ደግሞ ለመለኮታዊ ሥልጣናቸው እውቅና የሰጠ ሰነድ እንደነበረ የሚታወቅ ነው፡፡

ጸሐፊው ግን ይህ ትውፊት ለሰሎሞናዊያን ክርስቲያን መንግሥት ብቻ ሳይሆን ለዛጕዌ ነገሥታትም ጭምር ርዕዮት በመሆን ኢትዮጵያን በእስራኤል ተምሳሌት የተስፋ ምድር፤ ህዝቡንም በእግዚአብሔር የተመረጠና የተስፋይቱ ምድር ነዋሪ በሚል አስተሳሰብ በመቃኘት ‹‹ብሔረ ኢትዮጵያን›› ለማዋለድ አስችሏል በማለት ይሞግታል፡፡

በክብረ ነገሥት ላይ አያሌ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ደረሰ ከተነሳበት ክርክር አንጻር ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች በቅርቡ ለንባብ በቅተዋል፡፡ በሳባውያን ንግሥት እና የእስራኤል ንጉሥ ሰለሞን መካከል ተደርጓል ተብሎ የሚታሰበው ቃለ-ምልልስ ላይ በማተኮር በዘርፉ ባለሙያዎች ስለ እውቀት ፍለጋ እና ሽግግር የሚመለከተውን ንድፈ-ኃሳባዊ ጉዳይ ለመፈተሽ ማርያማ ማዕትካሬም የተባለች የባህል ጥናት ተመራማሪ እ.ኤ.አ. በ2002 ዓ.ም. ‹‹ሼባናይዜሽን›› በሚል ርዕስ ስር ጥናት አድርጋበታለች፡፡ ከዚህ ጥናት አስር ዓመታት በኂላ ዶናልድ ሌቪን ሰሎሞናዊያን የክብረ ነገሥትን ትርክት ቅቡልነታቸውን እንደሰበኩበትና የመንግሥታቸው ርዕዮተ-ዓለም እንዳደረጉት፤ እንዲሁም በሚያስተዳድሯቸው ግዛቶች የሚኖሩ ሕዝቦችን ብዝሃነት እውቅና በሚሰጥ መልኩ አሰባሳቢ ማንነት ለመፍጠር እንደተጠቀሙበት ያስረዳል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በመሰል ጥናቶች ላይ ፍላጎት አድሮበት ኃሳቡን ለማደራጀትና ሙግት ለመተለም በእጅጉ እንዳገዘው መረዳት ይቻላል፡፡ ያቀረበውም ሙግት ለዘርፉ ምሑራን እንግዳ አይደለም፡፡

ከክብረ ነገሥት ትውፊት የሚቀዳው አዜባዊነት ብሔረ-ኢትዮጵያን ለመፍጠር የፖለቲካ ፍልስፍና ግልጋሎት መስጠቱንና በበፖለቲካ አስተዳደር፣ የወታደራዊ አደረጃጀት፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ እና የመሬት ስሪት ሥርዓቶች ውስጥ ተሰናስኖ ጠንካራ የክርስቲያን መንግሥት ለመመስረት ጥቅም ላይ እንደዋለ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ክርክር ማቅረብ የሚቻል ቢመስልም ቅሉ፤ ይህንን ሙግት ግን በመረጃ አስደግፎ የጠነከረ ኃሳብ ለማቅረብ በእጅጉ አዳጋች ነው፡፡ የ15ኛው መ.ክ.ዘ. ሰነዶች የተሻለ እገዛ የሚያደርጉ ቢሆኑም የቀረበውን የንድፈ-ኃሳብ ክርክር ቅርፅ እና ይዘቱን ሊያጎለብት በሚችል ደረጃ ምሉዕ እና አስተማማኝ አይደሉም፡፡ ደራሲው የትውፊቱን መስፋፋትና ‹‹መስረፅ›› ለማስረዳት ያደረገው ሙከራ ቢደነቅም ትውፊቱ የማይመለከታቸው ኃይማኖታዊ ማንነቶች፣ የነገሥታቱ ‹‹ሰሎሞናዊነት›› ማንነት በንግሥና ዘመናቸው ከወሰዷቸው የፀኑ ፀረ-ይሁዲ እርምጃዎች ጋር ያለው ተቃርኖ (ambivalence)፤ ተገዳዳሪ ሙስሊም ኃይሎችን ለመመከት አስቻይ ትርክት እንዲሆን ተደርጎ ሲያበቃ በሙስሊሙ ማሕበረሰብ ዘንድ የሚኖረው ግምገማ፤ በወታደራዊ ቁጥጥር እና ግብር-ከፋይ አስተዳደር ስር ለዘመናት የቆዩና በአመዛኙ ራስ-ገዝ የነበሩ ግዛቶች ውስጥ የነበሩ ማሕበረሰቦች ይህንን ትውፊት ከነገሥታቱ ጋር የኃይማኖት፤ ቋንቋ እና ባሕል ቅርርብ ካለው የሰሜኑ ሕዝብ አንፃር በምን ደረጃ እንደሚጋሩት ያለመታወቁ፤ እንዲሁም ክብረ ነገሥት የሕዝቦችን አንድነት ለማምጣት ጥቅም ላይ ለመዋሉ ተጨባጭ መረጃ አለመኖር ወዘተ ተጨማሪ ምርምር የሚጠይቁ አከራካሪ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ሰሎሞናዊያን የተጠናከረ ማዕከላዊ መንግሥት (በደራሲው ቋንቋ ‹አሃዳዊ› መንግሥት) ለመመሥረት የክብረ-ነገሥትን አዜባዊነት ትውፊትን ተጠቅመውበት ነበር የሚለው የደራሲው

ክርክር የተማከለ መንግሥት ለመመስረት የሚያስችል ኃብት፣ ተቋም እና አሰባሳቢ ኃሳብ እንዳልነበራቸው የሚሞግቱን የዘርፉ ባለሙያዎች ትኩረት የሚሻ ነው።

በዚህም የሰሎሞናዊያን የመንግሥት ጥንካሬ ከወታደራዊ ኃይል፣ የመሬት እና ግብር ሐብት፣ እንዲሁም ከቤተ-ክህነት ድጋፍ ይመነጭ ነበር ለሚለው ግዙፍ የምሑራን ክርክር ትኩረት ያልተሰጠውን የርዕዮተ-ዓለም ፋይዳ ትንታኔ ቢያቀርብም ይህንን ነባር የክርክር ጭብጥ የሚሽር አይመስልም። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደራሲው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ታቦት ያነሳቸው እንግዳ ኃሳቦችና ክርክሮች ከታሪክ ምሑራን ይልቅ የስነ-መለኮትና ቀኖና ሊቃውንትን ጥልቅ ትኩረት የሚስቡ በመሆናቸው የዚህ ግምገማ አካል ሊሆኑ አይችሉም። ደራሲው ትኩረት ያደረገበት ይህ ክፍል የዳበረ ክርክር ስላልተደረገበት በደራሲው ሙግት ላይ የሚታየው አዜባዊነትን ሊሸከም ከሚችለው የማብራራት አቅም (explanatory power) በላይ ውስብስብ የሆኑ የሥርዓተ-መንግስት፣ የሕዝብና ሀገር ማንነት ጉዳይ የመተንተኛ መነፅር የማድረግ ዝንባሌዎች በከፊል የዚህ ውጤት ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

ይህ ከ13 እስከ 16ኛው መ.ክ.ዘ. ሰሎሞናዊያን የክርስቲያን መንግሥት የፖለቲካ አስተዳደር፣ የወታደራዊ አደረጃጀት፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ የመሬት ይዞታ ስሪት ሥርዓቶችና ርዕዮተ-ዓለም የሚዳስስ መጽሐፍ ለማዘጋጀት የታሪክ ጸሐፊው ቀዳማይ የታሪክ መረጃዎችን ተጠቅሟል። ለአብነትም የሰሎሞናዊያንና የኢማም አህመድን ዜና መዋዕሎች ፣ አጭሩን ታሪከ-ነገሥት፣ ገድላት፣ የአውሮፓውያን ተጓዦች የጉዞ ማስታወሻዎች፣ ለነገሥታቱ የተገጠሙ የሙገሳ ዘፈኖች፣ የጉልት ሰነዶች፣ የነገሥታቱ ደብዳቤዎችና እንዲሁም ነገሥታቱ ያዘጋጇቸውን መፅሐፍትና ሌሎች ቀዳማይ የታሪክ መረጃዎች ያጣቅሳል። በጉዳዩ ላይ የምሁራን የጥናት ውጤት የሆኑና በተለያዩ ቋንቋዎች (ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ጣሊያንኛ ወዘተ.) እንዲሁም የጥናት ዘርፎች (የታሪክ፣ አርኪኦሎጂ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ስነ-መለኮት፣ ቅርስ ጥናት እና ሌሎችም) የተደረጉትንም የምርምር ውጤቶችን ተጠቅሟል። በመጽሐፉ ማሳረጊያ ላይ ጠቋሚ መረጃ ስለያዘ አንባቢ የሚፈልገውን ቃል/ስም ገጹን ለማግኘት ስራውን ያቀልለታል። እነዚህ ጠንካራ ጎኖች ደራሲውን የሚያስመሰግነውና ከታሪክ ባለሙያ የሚጠበቅ ነው።

የመጀመሪያ እትም መሆኑ ብቻ ሳይሆን ብዙ ምሑራን በማይከጅሉት የጥናት ዘመን ላይ ምርምር ያደረገ መጽሐፍ እንደመሆኑ ከእንከኖች የጸዳ እንዲሆን አይጠበቅም። አንዳንድ የአርትዖትና የታሪክ መረጃ ግምገማ እና ዋቢ አደራረግ ችግሮች፣ እንዲሁም ከጥናቱ የዘመን እና ይዘት ዳራ ውጪ የሆኑ ኃሳቦች መካተት ተስተውለዋል። ለቀጣይ ሕትመት ግብዓት ይሆኑ ዘንድ በማሰብ እነዚህን ህፀፆች መጠቆም አስፈላጊ ነው።

የመጽሀፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ገፅ 1 ላይ መጀመር ሲገባው ገፅ 11 ላይ ይጀምራል። በተለያዩ ምዕራፎች ላይ የኃሳቦች መደጋገም ይታያሉ። በተለይ በአምደ ጽዮን እና ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥታት የደገኛው የክርስቲያኑ መንግሥት ከኢፋት-አዳል ጋር ያደረጋቸው ፉክክሮችና ጦርነቶች፣ እንዲሁም አዜባዊነትን በተመለከቱ ሀሳቦች ተደጋግመው ቀርበዋል። ‹‹የአዜባዊነት ርዕዮት ትውፊት›› በቂ ፅንሰ ኃሳባዊ ማብራሪያ ሳይቀርብበት ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ ጥቅም ላይ መዋሉና በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል የሆነው ምዕራፍ ስምንት ላይ መቅረቡ ለአንባቢው ግርታን ይፈጥራል። ከነበረው ታሪካዊ ፋይዳ አንጻር ካየነው መቅረብ ያለበት ሰሎሞናዊያን ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ የሚሉበት የዚህ መጽሐፍ የጊዜ መደብ መነሻ የሆነው የ13ኛው

መ.ክ.ዘ. ነው፡፡ በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ ቢቀርብ ድግግሞሹም ይታረማል፤ አንባቢያንም ስለጉዳዩ ጽንሰ ሐሳብ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡ ምዕራፍ ስድስት ላይ ያላለቁ ዓረፍተ-ነገሮች ይስተዋላሉ፡፡ (204፤ 234) ገፅ 213 ላይ በአረፍተ ነገሮች መካከል ‹‹ነገረ መለኮት›› የሚለው ቃል በስህተት ጎላ ተደርጎ ተፅፏል፡፡

የመረጃ ግምገማ እና የታሪክ መረጃ ዋቢ አደራረግ ችግሮችም አንዳንዶቹ የአርትዖት ክፍተት ውጤት ይመስላሉ፡፡ በዚሕ መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀሱ መረጃዎች መካከል በተለይም በዜና መዋዕሎች፤ ገድላት እና የጉዞ ዘገባዎች ላይ የገለልተኛነት፤ ተአማኒነት እና ለሳይንሳዊ ምርምር ያላቸው ፋይዳ ላይ ጥያቄ እንደሚቀርብ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህንን መልስ በሚሰጥ መልክ ቢያንስ ተደጋግመው በተጠቀሱት ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ላይ ግምገማ ሲደረግባቸው ግን አይታይም፡፡ የመጽሐፉ የግርጌ ዋቢ መጻሕፍት ማብራሪያዎች ቁጥራቸው ጠፍቶ በጥያቄ ምልክት (?) ተቀምጧል፡፡ ይህ ደግሞ የመረጃውን ምንጭ ለማመሳከር አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ቀድመውት የተቀመጡትን ሁለት የጥናት ውጤቶች ተከትሎ የተጻፈው ‹‹ዝኒ ከማሁ›› ከገፅ ቁጥር ጋር ሲጠቀስ ከሁለቱ የትኛውን እንደሚያመለክት ግልፅ አይደለም (ለምሳሌ ገፅ. 213፣ ግርጌ ቁጥር 462)፡፡ ደራሲው አንድን ጥናት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቅሰውና በግርጌ ዋቢ ሲያደርግ የጥናቱን ጸሐፊ፤ የጥናት ርዕስ፤ የታተመበትን ሀገርና አሳታሚ እንዲሁም የታተመበትን ዓመት መግለፅ እንደሚገባው ይታወቃል፡፡ ይሁንና በአጭሩ የደራሲውን ስም እና የታተመበትን ዓመት ብቻ በማስቀመጡ ስለጥናቱ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ከዋቢ መፃህፍት እንድናመሳክር ያስገድዳል፡፡ ደራሲው ዋቢ-መጻሕፍት ከተካተተ በግርጌ ማስታወሻ ላይ በአጭሩ ማስቀመጥ የሚፈቅደውን የቺካጎ ፎርማትን የተጠቀመ ቢመስልም ብዛት ባላቸው ገጾች ግርጌ ላይ ግን ሙሉ ዋቢ ስላቀረበና የዚህን ፎርማት ሲተገብረው ስለማይታይ አጠቃቀሙ ወጥነት እንዲኖረው ይጠበቅ ነበር፡፡

በመጽሐፉ ከተቀመጠው የጊዜ ዘመን እና ይዘት አንፃር አንዳንድ የደራሲውን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ይታያሉ፡፡ ስለኦሮሞ ሕዝብ የቀረበው ዘለግ ያለ ሐቲት ተገቢነቱና ዓላማው ግልፅ አይደለም፡፡ በክርስቲያናዊው መንግሥት ስር በነበሩ ግዛቶች ይኖሩና ይተዳደሩ የነበሩ ሕዝቦች ማንነት ባልቀረበበት በዚህ መጽሐፍ የኦሮሞ ሕዝብን ማንነት እና ሚና ላይ የተደረጉ ምርምሮች ላይ የተናጠል ግምገማ ማድረጉ ግርታን ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም ደራሲው በቀጣይ ሊያቀርብልን ባሰበው ጥናቱ ይሕንን በብዙ ምሑራን ምርምር የተደረገበትን የኦሮሞዎች ታሪክ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን ስለሚገልጽ በዚሁ ቀጣይ ስራው ውስጥ ቢካተት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

አንዳንድ ጉዳዮች ከመፅሐፉ የታሪክ ምርምር አውድ ውጪ ቢሆኑም ደራሲው ባልተለመደ መልኩ በዝርዝር አቅርቦ ሲሞግታቸው ይታያል፡፡ በምዕራፍ አንድ ላይ የቀረበው በዋሻ ውስጥ የተገኙ ያልበሰበሱ አስከሬኖች ጉዳይ፤ ምዕራፍ ስድስት ላይ ስለ ታቦት ስርዓት፤ እንዲሁም የታቦት ተንቀሳቃሽነት በነባር እምነቶች ከነበረው ተንቀሳቃሽ ቁሶች ጋር ያለውን መወራረስ ለማሳየት የቀረበውን ክርክር የተመለከቱ ዝርዝር ኃሳቦች ደራሲው ልዩ ትኩረት የሰጣቸው ናቸው፡፡ ይሁንና ወቅታዊ የሥነ-መለኮት ክርክሮችን በሚነካ መልክ መቅረባቸው ብቻ ሳይሆን የመጽሐፉ የምርምር ትኩረት አንጻር ጠቃሚነታቸው አይታይም፡፡ የደራሲውንም የታሪክ እውነት ፍለጋ እና ሚዛናዊነት ሲፈትኑት ይታያሉ፡፡ መሰል አከራካሪና ወሳኝ ያልሆኑ

ጥያቄዎች ላይ አላስፈላጊ ትኩረት ባይሰጥ የመጽሐፉ አንጻራዊ አካዳሚያዊ ይዞታ የተጠበቀ ይሆናል፡፡


አውግቸው አማረ፤ ፒ ኤች ዲ

የታሪክ መምህርና ተመራማሪ

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ